የሰ/መ/ቁ.108692

ታህሳስ 24 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሀመድ

ተኽሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ሡናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- የትግራይ ክልል ዐቃቤ ህግ

ተጠሪ፡-አቶ ገብረአርዕያ አሰፋ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው አመልካት በሥልጣን አላግባብ የመገልገል የደንብ መተላለፍ ጥፋት አልፈፀመም በማለት የትግራይ ክልል ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? ሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ የታየው በሐውዜን ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪና ሌሎች በዚህ ክርክር ተሣታፊ ያልሆኑ ሰዎች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 796 የተመለከተውን በመተላለፍ፤ ሐውዜን ከተማ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ሆነው ሲሰሩ መጣራት የሚገባውን ነገር ሣያጣሩና አቶ ሃይላይ ገራስና ወ/ደብረብርሃን አረጋዊ እህታቸው እንደፈረሙ በማሰብ ፈርመናል ብለውናል በማለት ግንቦት 7 ቀን 2009 ዓ.ም ዕርቅ በማፅደቅና የአቶ ሃይላይ ገራስ ጋብቻ ፈርሷል የሚል ማስረጃ ለመቀሌ ማዘጋጃ ቤት በመላካቸው በሥልጣን አላግባብ ወንጀልፈፅመዋል የሚል ክስ አቅርቧል፡፡
2. ተጠሪ በአመልካች የቀረበበትን የወንጀል ክስ ክዶ ተከራክሯል፡፡ አመልካች ሶስት ምስክሮች በማቅረብ፤ ከተጠሪ ፊት ያልቀረቡት አቶ ሀይላ ገራስና ወ/ደብርሃን አረጋዊ ለማህበራዊ ዳኞች ፊት ቀርበው ሣይፈርሙ፤ የፈረሙ በማስመሰልና የዕርቅ ሰነድ በማፅደቅ ለመቀሌ ማዘጋጃ ቤት ማስረጃ ልኳል በማለት የመሰከሩ ሲሆን፤ የፅሑፍ ማስረጃም አመልካች አቅርቧል፡፡ ተጠሪ የመከላከያ ማስረጃ አቅርቧል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ የተጠቀሰበትን

የወንጀል ህግ አንቀጽ 796 በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ ነው በማለት በሁለት ወር እስራት ተጠሪ እንዲቀጣና ቅጣቱ በሁለት ዓመት የሙከራ ጊዜ እንዲገደብ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሣኔ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አፅንቶታል፡፡

3. ተጠሪ የበታች ፍርድ ቤቶች በሰጡት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ሰበር ችሎት የሰበር አቤተታ አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ተጠሪ በህግ የተሰጠውን ሥልጣን አላግባብ ስለመገልገሉ፣ የአመልካች ተጠሪ ፈፅሞታል በማለት የሚዘረዝረው የተረጋገጠው ፍሬ ነገር አያሳይም፡፡ የተጠሪ ተግባር ወንጀል የሚያቋቁም አይደለም በማለት ተጠሪ ከተሰሰበት ወንጀል በነፃ እንዲሰናበት በማለት ውሣኔ ተስቷል፡፡ አመልካች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ታህሳስ 21 ቀን 2007 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበሲሆን፣ ተጠሪ የወ/ሮ ምፅላል ወላጆች ያልፈረሙበትን ሰነድ እንደፈርሙበት በማስመሰልና በችሎት ሣይቀርቡ ቀርበዋል በማለት ማስረጃ መስጠቱ፤ በግል ተበዳይ ላይ ጉዳት ማድረሡ በተረጋገጠበት ሁኔታ ተጠሪ የወንጀል ተጠያቂነት የለበትም መባሉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ መምህር የማነብርሃን እና ወ/ሮ ምፅላል ሃይላይ የሥጋ ዝምድና ያላቸው መሆኑን በፖሊስ ጣቢያ ከተካሰሱ በኋላ ቤተዘመድ የተራቁ መሆኑን በመግለፅ የሰጠሁት ማስረጃ ስህተት የለበትም በወንጀልም አያስጠይቀኝም በማለት ግንቦት 17 ቀን 2007 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡

   አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

4. ከሥር የጉዳዩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 796 የተመለከተውን በመተላለፍ ጥፋት ፈፅሟል በማለት ክስ የቀረበበት፣ ተጠሪ ከሌሎች ሁለት ሰዎች ጋር ሆኖ የሀውዜን ከተማ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኛ ሆኖ ሲሰራ፣ መምህር የማነብርሃን ከወ/ሮ ምፅላል ሃይላይ ጋር ጋብቻ የሚከለክል የሥጋ ዝምድና ያላቸው መሆኑን የሚገልፅ ግንቦት 17 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ የዕርቅ ሰነድ በማፅደቅ መጋቢት 2 ቀን 2002 ዓ.ም ከተፃፈ ከመሸኛ ደብዳቤጋር ለመቀሌ ማዘጋጃ ቤት ልከዋል በማለት ነው፡፡

   ተጠሪና ሌሎች የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች አፀደቁት የተባለው የዕርቅ ሰነድ መነሻው በሐውዜን ከተማ ፖሊስ ጣቢያ ያቀረበን የወንጀል ክስ ቀሪ ለማድረግ፤ የወንድና የሴት ቤተዘመዶች ሶስት ሽማግሌዎች ባሉበት የታረቁ መሆኑን የሚገልፅናከአንደኛ እስከ አምስተኛ ስማቸው የተገለፀው ሰዎች የፈረሙ መሆኑን የሚገልፅና 6ኛ ምፅላል ሃይላይ አልፈረመችም የሚልና የአስታረቁትን ሶስት ሰዎች ስም የያዘ መሆኑንና ተጠሪ

ከሌሎች የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ጋር በመሆን የምስክሮችን ቃል ሰምቶ፤ ማስረጃ የሰጠ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

5. አመልካች የሚከራከረው ተጠሪ ከሌሎች ማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ጋር ሆኖ ማጣራት የሚገባውንና ፍሬ ነገር ሣያጣራ በወቅቱ የዕርቅ ሰነዱን ለማፅደቅ በማህበራዊ ፍርድ ቤት ያልቀረቡ የወ/ሮ ምፅላል ሃይላይ ወላጆች፣ ችሎት የቀረቡ መሆኑን በአግባቡ ሣያረጋግጥ፣ በችሎት እንዲቀርቡ በማስመሰል ማስረጃ ሰጥቷል በማለት ነው፡፡ ተጠሪ ከሌሎች የሀውዜን ከተማ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ጋር በመሆን፣ ምስክሮችን በመስማት መምህር የማነብርሃን ወ/ሮ ምፅላል ሀይላይ በትግራይ ክልል የቤተሰብ ህግ መሠረት ጋብቻ እንዳይፈፅሙ የሚከለክል የሥጋ ዝምድና ያላቸው መሆኑን በመግለፅ፣ የዕርቅ ሰነዱን የምስክሮች ቃል ያረጋገጡ መሆኑን ገልፀው ለመቀሌ ማዘጋጃ ቤት ማስረጃ መስጠታቸው ተረጋግጧል፡፡

6. ተጠሪ ማስረጃውን አጣርቶ የሰጠው ከሌሎች የሀውዜን ማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ጋር በመሆንና በችሎት በመሰየም እንደሆነ በመከላከያ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ የሀውዜን ከተማማህበራዋ ፍርድ ቤት ዳኞች /ተጠሪን ጨምሮ /ይህንን ማስረጃ የሰጡት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37 ንዑስአንቀጽ 1 1985 በወጣው የትግራይ ክልል ሕገ መንግስት 89 እንደተሻሻለ እና በትግራይ ክልል ምክር ቤት ባወጣው የቤተሰብ ሕግ መሠረት በተሰጣቸው የዳኝነት ነክ ሥልጣን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ይህ ከሆነ፣ ተጠሪ በሕግ የተሰጠውን የዳኝነት ነክ ተግባሩን ከሌሎች ዳኞች ጋር በሚወጣበት ወቅት፤ የፍርድ ሥራ ስህተት በይግባኝ፤ በሰበር ወይም በሌላ በሕግ በተዘረጋ የፍርድ ሥራ ስህተት ማረሚያ መንገዶች የሚመለከታቸው ግለሰቦች አቅርበው እንዲያሳርሙ ከሚደረግ በስተቀር፣ ተጠሪ በተናጠል የወንጀል ህግ አንቀጽ 796 በመተላለፍ በሥልጣን አላግባብ የመገልገል ወንጀል ፈፅሟል በማለት የወንጀል ክስ የሚቀርብበትና ኃላፊ የሚሆንበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ከዚህ አንፃር የትግራይ ክልል ሰበር ችሎት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በመሻር ተጠሪ በነፃ እንዲሰናበት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 67011 ጥቅምት 14 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡